# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 256 ሚያዚያ 3 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ነጻነት ንቅናቄ በህዝባችን እየደረሰ ያለውን መፈናቀልና እልቂት ለማስቆም የሚያደርገውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል። የዲሞክራሲ ሃይላት ድርጅቶችም ሆነ የሀገራችን ወጣቶች፤ የአማራውና የተቀረው ህዝባችን ጮኸትና ዋይታ በደልና ሰቆቃ በሁሉም የሀገራችን ህዝቦች እየደረሰ ያለ ጥቃት ነውና ለጥሪያቸው የማያዳግም መልስ ለመስጠት ትግሉን ትቀላቀሉ ዘንድ ጥሪያችን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የኢትዮጵያ አደገኛ የፖከቲካና ማህባዊ ጉዞ ያሳሰባቸዉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት እራሰቸዉን በህቡዕ እያደራጁ መሆኑ ተነገረ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት የተከተላቸዉ የፖለቲካ፤የኤኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ያደረሰዉ ጥፋትና አሁንም አገሪቱ የምትጓዝበት አደገኛ አቅጣጫ ያሳሰባቸዉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት እራሳቸዉን በህቡዕ እያደራጁ መሆኑን አንድ ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኘዉ የዚሁ የህቡዕ ድርጅት ህዋስ መሪ ከግንቦት ሰባት ድምጽ ጋር ባደረጉት የስልክ ምልልስ ገለጹ። እኚህ ለደህንነታቸዉ በመስጋት ቃለምልልሳቸዉ በሬድዮ እንዳይደተላለፍ የጠየቁን ከፈተኛ የጦር መኮንን በህቡዕ የመደራጀቱ እንቅስቃሴ ሠራዊቱ በብዛት በሚገኝባቸዉ ቦታዎች ሁሉ እየተካሄደ ሲሆን በቅርብ ግዜ ዉስጥ ከሌሎች ለለዉጥ ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር በመሆን ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚጀምሩ ተናግረዋል።

የዚህ “አገርህን አድን” በሚል ስያሜ የሚጠራዉ አገር ወዳድ ቡድን አባላት የወያኔ ደህንነት የሚያደርግባቻዉን የሃያ አራት ሰአት ክትትል ጥሰዉ ለመጀመሪያ ግዜ የተሰባሰቡት ከአራት አመታት በፊት ሲሆን ያሰባሰባቸዉም ወያኔ ሠራዊቱ ዉስጥ የሚከተለዉን ጭፍን የዘረኝነት ፖሊሲ ለመቋቋም እንደሆነ ታዉቋል። ሆኖም ይህ በ“አገርህን አድን” ቡድን ስር በመደራጀት ላይ የሚገኘዉ ሠራዊት አላማ የሠራዊቱን መብትና ነጻነት አስጠብቆ ወደ ሠፈሩ መመለስ ሳይሆን የቡድኑ ተቀዳሚ አላማ ለህዝብ በገባዉ ቃል መሠረት ኢትጵያንና ህዝቧን ከወያኔ ዘረኝነትና ከፋፍለህ ግዛዉ ፓሊሱ ማዳን ነዉ ሲሉ የቡድኑ ቃል አቀባይ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዛሬም በጽናት ትግላቸውን ቀጥለዋል በትናንትናው እለትም ፍትህ ይሰጠን በማለት ተቃውሞ ሲያሰሙ ዋሉ

ላለፉት አስራ አራት ወራት በጽናት ድምጻችን ይሰማ የሚል መፈክር አንግበው ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ አስጨንቀው የሚገኙ ሙስሊሞች በትናንትናው እለትም ተቃውሞአቸውን በመቀጠል የፍትህ ይሰጠን ጥያቄአቸውን ሲያሰሙ መዋላቸውን ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገለጠ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያኑ ቀደም ብሎ ሲያሰሙ ከነበረው የድምጻችን ይሰማ ጥያቄ ለወጥ ባለ መልኩ ፍትህ የሚል መሪ ቃልን ሲያሰሙ መዋላቸው ታውቋል።

በትናንትናው እለት በአዲስ አበባ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች "ፍትህ" የሚል ጽሁፍ የያዙ ወረቀቶችን በመያዝ ፍትህን በማለት ሲጠይቁ መዋላቸውን የገለጠው ዘጋቢያችን ፤ ፍትህ አጥተው በእስር ቤት የሚሰቃዩ መሪዎቻቸውን እጃቸውን በማጣመር በድጋሜ ሲያስቡ መዋላቸውን ገልጧል። እንደተለመደው በዚሁ የተቃውሞ ድምጽ አካባቢ በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት ቢታዩም፣ ምንም አይነት ግጭት አለመፈጠሩን የደረሰን ሪፖርት አመልክቷል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በዘገባው እንዳመለከተው በአዳማ ፍትህ የጠየቁ ሙስሊሞች በፖሊሶች ተደብድበው እንዲባረሩ የተደረጉ ሲሆን በእስር ላይ በሚገኙት ሙስሊም መሪዎች ላይ ምንም አይነት ጠንካራ የሰነድም ሆነ የሰዎች ማስረጃ አለመቅረባቸውን ገልጧል።

## ወያኔ የምረጡኝ ቃለ መሃላ እያስፈጸመ መሆኑ ተሰማ፣ የአዲስ አበባ ሴቶች ቃለ ማህላ ፈጸሙ

ትናንትናው እለት በአዲስ አበባ የሚኖሩ ሴቶች በአዲስ አበባ ስታዲየም በመገኘት ኢህአዴግን እንመርጣለን የሚል ቃለ መሃላ እንዲፈጽሙ መደረጋቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

ወያኔ ኢህአዴግ ያለጠንካራ ተቃዋሚ በሚሮጥበት የአዲስ አበባ እና የክልል ምርጫ በአዲስ አበባ ሴቶች ሊግ አማካኝነት የቤት ለቤት ቅስቀሳ እና ማስፈራሪያ ሲያደርግ መቆየቱን የገለጠው ዘጋቢያችን ቃለ መሃላ ለመፈጸም የወቱት ሴቶች በነፍስ ወከፍ ኮፍያ እና (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የ አማራ ተወላጆችን አሁንም ለተጨማሪ ጥፋት እያዘጋጀ መሆኑ ታወቀ

ለረጂም ዘመናት ከ አካባቢው ህብረተሰብ ጋር ተዋደውና ተግባብተው ይኖሩ የነበሩ የ አማራ ተወላጆችን ኢ ሰብ ዊ በሆነ መንገድ እንዲፈናቀሉና በሰላምም ይኖሩበት ከነበረው ህበተስብ ጋር ግጭትና እንዲፈጥሩ ያደረገው ዘረኛ አገዛዝ እነኝህን ተፈናቃዮች እንደገና በመመለሱ ለሌላ ጥፋት እየተዘጋጀ መሆኑን ዘጋቢያችን ከባህር ዳር በላከልን ዘገባ አመለከተ።

ቁጥራቸው ከ5 ሺ በላይ የሚጠጉ ከፍኖተሰላም ወደ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እንዲመለሱ የተደረጉት የአማራ ተወላጆች በሚመለሱበት ቦታ የደህንነት ዋስትና እንደሌላቸው እየገለጡ ሲሆን መሰሪው አገዛዝ በበኩሉ ስህተት መፈጠሩን በማመን ችግሩን የፈጠሩት ታች ያሉ ባለስልጣናት ነው የሚል አሳፋሪ መልስ በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

ከትናንት በስቲያና፣ በትናንትናው እለት መኪኖች ተፈናቃዮችን ከአቅማቸው በላይ በመጫን ወደ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ማቅናታቸውን የገለተው ዘጋቢያችን የክልሉ ሆድ አደር ባለስልጣናት ተፈናቃዮች እንዲወጡ የተደረገው በስህተት መሆኑን ተናግረው ይቅርታ ጠይቀዋል ብሏል። የአማራ ክልል ፕሬዘዳንት ተብየውም የዞንና የወረዳ አመራሮችን ተጠያቂ ያደረጉ ሲሆን፣ እርምጃ እንደሚወሰድባቸውም መዛቱ ታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው "እርምጃ ይወሰድባቸዋል የተባሉት የከማሽ ዞን አስተዳዳሪ እና የያሶ ወረዳ አስተዳዳሪ" መሸፈታቸውን የሚገልጥ መረጃ የደረሰው መሆኑን አመልክቷል። ባለስልጣኖቹ " የአካባቢውን ተወላጆች አማራ ወረራችሁ ተነሱ እያሉና እየሰበኩ ወደጫካ መግባታቸውን የደረሰው መረጃ ያመለክታል ያለው ኢ ሳት የፌደራል ፖሊሶችም የሸፈቱትን ባለስልጣናት በመፈለግ ላይ መሆናቸውን አክሎ ገልጧል።

በከማሺ ዞን በአንድ የግብርና ኢንቨስትመንት ስራ ውስጥ ተቀጥረው እስካሁን ያልተፈናቀሉ የአማራ ተወላጅ እንደገለጹት በክልሉ እየተነዛ ያለው ወሬ አደገኛ በመሆኑ ተፈናቃዮች ሲመለሱ ችግር ሊደርስባቸው እንደሚችል ስጋታቸውን መግለጻቸውን ኢሳት አክሎ ዘግቧል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአማራ ተወላጆችን ማፈናቀሉን እንደቀጠለ መሆኑ ታወቀ

የዘረኝነት አባዜ የተጠናወተው የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ በቤሻንጉል ጉምዝ ነዋሪ የነበሩ የአማራ ተወላጆችን ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ማፈናቀሉ ሳያንሰው ይህን ድርጊቱን ወደ ደቡብ ክልል በማዞር በዚሁ ክልል የሚገኙ የአማራ ተወላጆችም በድጋሜ እንዲለቁ እያደረገ መሆኑን ዘጋቢያችን በሃገር ውስጥ የሚታተም ጋዜጣን ዋቢ በማድረግ በላከልን ሪፖርት ገለጠ።

ዘጋቢያችን እንደገለጠው፣ ቀደም ሲል በቤንች ማጂ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ የተፈናቀሉ ከ20 ሺ ያላነሱ አርሶደሮች የገቡበት ሳይታወቅ፣ አሁን ደግሞ በዚሁ ዞን በሚኒት ወልድያ ወረዳ በተለይም ዘንባብና አርፋጅ ቀበሌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ከ350 በላይ የአማርኛ ተናጋሪዎች ተፈናቅለው በወረዳው አካባቢ በሚገኝ ጫካ ውስጥ ተጠልለው ይገኛሉ በማለት ፍኖተ ነጻነት የተሰኘ ጋዜጣ መዘገቡን ገልጧል።

እንደፍኖተ ነጻነት ዘገባ ተፈናቃዮቹ ከመኖሪያ አካባቢያቸው 61 ከብቶችና ግምቱ ያልታወቀ እህል ተዘርፈው አካባቢያቸውን ጥለው ለመውጣት የተገደዱት ሲሆን ተሸሽገው ባሉበት ጫካ ለከፍተኛ ርሃብና ውሃ ጥም መዳረጋቸውንም ጋዜጣው መዘገቡን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጧል።

ከተፈናቃዮች መካከልም 4 ሰዎች በግፍ መገደላቸውንና የወረዳው አስተዳደር አካላት “እናጣራለን” ከማለት ውጭ ምንም መልስ ባለመስጠታቸው ጉዳዩ እየባሰ በመሄዱ ንብረቶቻቸው ተዘርፈው በአሁን ወቅት ለዓመታት የኖሩበትን አካባቢ ጥለው በጫካ መጠለልን መርጠዋል ብሏል ጋዜጣው።

ተፈናቃይ የአማራ ተወላጆችም በአሁን ወቅት ከወረዳው ፖሊሶች ውጭ የአስተዳደሩ አካላት በግፍ መፈናቀላችንን በተመለከተ ያላቸውን ውሳኔ እንዲያሣውቁን ብንጠይቅም ምላሽ የሰጠን ባለመኖሩ አሁንም ለከፍተኛ ችግር በመጋለጣችን የሚመለከተው የመንግስት አካል ምላሽ እንዲሰጠን እንፈልጋለን ማለታቸውን ጋዜጣው መዘገቡን ዘጋቢያችን ገልጧል።

ቀደም ሲል በዚሁ ክልል የተፈናቀሉ አብዛኞቹ ዜጎች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በብሄር ከፍፈሎ መግዛት የዛገ ፖሊሲ ነዉ!

በሀገራችን ኢትዮጵያ የዜጎች የመዘዋወር፣ ንብረትን የማፍራት፣ የመኖር፣ የመናገር፣ የመምረጥ እና የመመረጥ መብቶች የሚወሰነው በጥቂት የህወሃትና ጀሌ ባለስልጣኖች መልካም ፈቃድ እንጅ በመሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ድንጋጌ አይደለም።

በሩዋንዳ የተፈጸመው የሰውልጅን ዘር የማጥፋት ድርጊት፣ በሀገራችንም ኢትዮጵያ በህወሃት ኢህአዴግ አማካኝነት እየታየ ነው። ዜጎች በማንነታቸው ከየት አካባቢ/ ብሄር/ ዘር ማንዘር ነው የመጣኸው/ሽው? እዚህ ለመኖር፣ ለመስራት፣ ንብረት ለማፍራትና ለመሳሰሉት የመኖሪያ ፈቃድ አለህ/ሽ ወይ? በሚል ብሄርን ከፋፍሎ መለያ በመስጠት ተከባብሮ የኖረን ህዝብ በትውልድ ሀገሩ እርስ በርሱ ለማጋጨት እየተደረገ ያለው የዛገ የፖለቲካ ፖሊሲ የሀገራችንን ህልውና እየተፈታተነ ነው።

በብሔር ብሔረሰብ ክፍፍል ላይ የተመሰረተ ዘርን በማጥፋት ፖለቲካ የተጠመዱት ወያኔዎች፣ እንደ ሰደድ እሳት በአገራችን ዜጎች ላይ ያላቸውን ጥላቻ ከወዲያ ወዲህ እየሄዱ ያሳዩናል። በተለይም በአማራው የተጀመረው የበቀል ርምጃ ቀጥሎና ተባብሶ የጥፋት በትራቸው የገረፋቸው የኦጋዴን፤ የጋምቤላ፤ የደቡብ ክልል፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የዋልድባ አባቶች የቅርብ ግዜ በደሎች ሳይረሱ ከበደል ላይ በደል፣ ከጩኸት ላይ ጩኸት እየጨመረ በማን አለብኝነት የጀመረውን ዘርን የማጥፋት አባዜ ቀጥሎበታል።

የዜጎችን ሰዋዊ መብት ወያኔ በጠበንጃ ሃይል ጉልበት በመተማመን ንብረትን ቀምቶ፤ ነፍሰጡርንና አራስን አፈናቅሎ፣ ህጻናትን ሜዳ ላይ በትኖ ማባረር፣ የድብደባና የግድያ ወንጀሎች በአማራው ሕዝብ ላይ መፈጸሙ አዲስ ያልሆነና ከበፊቱም የነበረውን የወያኔን የከፋፍለህ ግዛ የዛገ ፖሊሲ ተግባራዊ እያደረጉት እንደሆነ ያሳየ ምልክት ነው። ይህ ዓይነቱ ዘግናኝ ወንጀል በተለያዩ ጊዜያትና አካባቢዎች በተለይም በኦጋዴን፣ በአኝዋክ፣ በኦሮሞ፣ በደቡብ፣ በአፋር፣ በሙርሲ እና በሌሎችም የማህበረሰባችን ክፍል ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ተፈጽሟል። አሁንም እየተፈጸመ ነው።

ህወሃት/ኢህአዴግ ይህንን የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈጽመበት ዋናው ምክንያት የአንድን ዘር የፓለቲካ፣ የኤኮኖሚና ወታደራዊ የበላይነቱን ለማስጠበቅ ስለሆነ፤ ለዚህ እኩይ ዓላማው መሳካት እንቅፋት ናቸው ብሎ በሚገምታቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ወደፊትም ተመሳሳይ እርምጃ ከመፈጸም እንደማይቆጠብ እየነገረን ነው።
ይሁን እንጅ ወያኔና አበሮቹ ይህ ዘርን የማጥራት (Ethinc Cleansing) ወንጀል ሲፈጽሙ በየትኛውም ግዜና ዘመን ከተጠያቂነት ወይም በወንጀል ከመፈለግ እንደማይድኑ የተረዱ አልመሰለንም።

የወያኔን የዘር ማጥራት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚቃወመዉ እና በተለይም አማራዉ ከትውልድ ቀዬው በግዳጅ ተባሮ ለጎዳና ተዳዳሪነት ሲዳረግ የተመለከተ የአካባቢዉ ነዋሪ ህዝብ በፍጹም ወያኔን ያልደገፈና ያልተባበረ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ማፈናቀሉን ተቃዉሞ ተፈናቃዮቹን እንባ እያፈሰሰ፣ ለስደት ጉዟቸው ይሆን ዘንድ ራሱ አማራው አርሶና ቆፍሮ እሸት ካፈራበት ማእድ ወይም የዛሬ የበይ ተመልካች ከሆነበት ማሳ ስንቅ እየቋጠረ ነበር የሸኛቸው።

ለብዙ አመታት አብረዉ ከመኖራቸዉ የተነሳ የአብሮ መኖር ኢትዮጵያዊነት መንፈስ የገነቡና በጋብቻና በማህበራዊ ኑሮ የተሳሰሩ ዜጎች በወያኔ ፖሊሲ ምክንያት ሳይፈልጉ ሲለያዩ ማየት ምን ያህል አሳዛኝ መሆንን የኢትዮጵያ ህዝብ ይረዳል።

በሌሎች አለማት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት የስደት ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት በፍርድ ቤት እና በተለያዩ ሚዲያዎች የመኖር መብታቸው ይከበር ዘንድ ሲከራከሩ፤ እነህ ምስኪን የሀገራችን ዜጎች ግን በትውልድ ሀገራቸው፣ መንደራቸው የመኖሪያ ፈቃድ ተነፍጓቸው፣ ይህንንም እንዳይጠይቁ ሆነው ይባረራሉ።

ታዲያ ይህንና ሌሎች በህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን በደሎች በጋራ ሆነን ለመታገል እንዲሁም ለአለም ድምጻችን ለማሰማት ኢትዮጵያዉያን ለብዙ ግዜ በትላልቆቹ የአገራችን ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም መያዝ አቅቶን ብዙ ዘመን ቆይተናል:: አሁን ግን ሌላ ቢቀር ከምን ግዜም በተሻለ ሁኔታ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች በኢትዮጵያ አንድነትና በዚህ አንድነት ዉስጥ መመስረት ሳለለበት የዲሞክረሲ ስርአት የጋራ አመካከት መጥቷል።

ይህንን ኢትዮጵያዊ አንድነት የጋራ ትግልና የዜጎችን ሁለንተናዊ መብት የማስጠበቅ የነጻነት ትግልን ትብብር እውን እንዲሆን ባለፈው ግዜ በከማል ገልቹ የሚመራዉ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባር ከሁለት አመት በፊት የወሰደዉ የአቋም ለዉጥ እና በቅርቡ ደግሞ በኦነግ ታሪክ ዉስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸዉ ሰዎች የወሰዱት ተመሳሳይ አቋም የሚያሳየዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን በብሄር ከፋፍለህ ቅጣዉ ፖሊሲ ከኢትዮጵያ መወገድ እንዳለበት እና በሁሉም ወገናችን የሚደርሰው በደል ሰቆቃና ስደት የሁሉም ፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ መሆኑንና በጋራ ሆነን የዛገን የወያኔን የዘር ማጥራት ፖሊሲ የምናስቆበት፣ ለአንዴ ለመጨረሻ ግዜ ታግለን የምናስወግድበት ሰአት ላይ ነን።

በተጨማሪ ወያኔ አገራችንን በብሄር መነጽር ብቻ የሚመለከትበትን መንገድና የሚሸርበዉ ሴራ በብሄር የተደራጁ ድርጅቶችንም እያንገሸገሻቸዉ መምጣቱን፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን ወያኔን የማስወገድ እና ኢትዮጵያን የማዳን የትግል ደወል ጥሪ ላይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ስለሆነም ግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ነጻነት ንቅናቄ በህዝባችን እየደረሰ ያለውን መፈናቀልና እልቂት ለማስቆም የሚያደርገውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል። የዲሞክራሲ ሃይላት ድርጅቶችም ሆነ የሀገራችን ወጣቶች፤ የአማራውና የተቀረው ህዝባችን ጩኸትና ዋይታ በደልና ሰቆቃ በሁሉም የሀገራችን ህዝቦች እየደረሰ ያለ ጥቃት ነውና ለጥሪያቸው የማያዳግም መልስ ለመስጠት ትግሉን ትቀላቀሉ ዘንድ ጥሪያችን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## የኢትዮጵያ አደገኛ የፖከቲካና ማህባዊ ጉዞ ያሳሰባቸዉ የመከላከያ ሰራዊት

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ አገዛዝ በአማራዉ ወገናችን ላይ የሚያደርሰዉን ጥቃት በቅርብ እየተከታሉት እንደሆነ የተናገሩት እኚሁ ቃል አቀባይ እንደዚህ አይነቱን የማን አለብኝነት ወንጀልና ባጠቃላይ የወያኔ ዘረኞች በግልጽ የሚያካሄዱት መብት ረገጣ፤ግድያ፤ዝርፍያና የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ለባዕዳን አሳልፎ መስጠት ወያኔ አስካልተወገደ ድረስ የማይቆም በመሆኑ ያለን አማራጭ በቻልነዉና በምናዉቀዉ መንገድ ሁሉ ወያኔን ለማስወገድ መታገል ዋናዉ አላማችን ነዉ ብለዋል።

በመጫረሻም ከነማን ጋር ትሰራላችሁ ተብሎ የተጠየቁትን ጥያቄ ሲመልሱ ዛሬ አገራችን ለመዉደቅ በመንገዳገድ ላይ በምትገኝበት ወቅት ያለን አማራጭ አልገዛም ካለና የእኩሎች አገር የምትሆን ኢትዮጵያን ለመገንባት ፍላጎቱና ቆራጥነቱ ካላቸዉ ወገኖች ጋር ሁሉ አብረን እንታገላለን ብለዋል። በአሁኑ ወቅት አያሌ ኢትዮጵአዉያን ወያኔን ለመታገል መሳሪያ ካነሱ ወገኖች ጋር በየቀኑ እየተቀላቀሉ ስለሆነ የኛም አላማ የትግል ስልትና የተለየ የትግል ቦታ ሳንመርጥ ወያኔን ያዋጣናል ባልነዉ ስልትና ይመቸናል ባልነዉ ቦታ ሁሉ እስከእለተ ሞቱ እንታገለዋለን ብለዋል።

---

## ወያኔ የምረጡኝ ቃለ መሃላ እያስፈጸመ መሆኑ ተሰማ፣ የአዲስ አበባ ሴቶች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቲሸርት የታደላቸው ሲሆን አንዳንዶቸች አበል እንደተከፈላቸውም ታውቋል። በተለያዩ መኪኖች ላይ ቅስቀሳ ያደርጉ የነበሩ ሴቶች ህዝብ የሰለቸውን የመለስ ዜናዊን ፎቶ የያዙ ቲሸርቶችን በመልበስ እንዲሁም ፎቶግራፋቸውን በመያዝ እንደግፋለን ሲሉ መዋላቸው ታውቋል። ይህን ቃለ መሃላ ከፈጸሙት ሴቶች ውስጥ አንዷን አዛውንት ያናገረው ዘጋቢያችን እንደገለጠው፣ ሁሉም ቃለ መሃላ ፈጻሚ ሴቶች ሙሉ በሙሉ በጥቅም ተገዝተው እንጂ ከልብ የወያኔ አገዛዝ ድጋፍ ኖሯቸው እንዳልሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ ያውቃል ማለታቸውን ገልጧል።

---

# በደል እንዴት ይረሳል!!

አማኑኤል አጋላ የህይወትን ለዛም ይሁን መዘዝ ገና በዉል ለይቶ ያላወቀ የ14 አመት ልጅ ነዉ። እህቱ ማጂን እሷም ብትሆን ወንድሟን አመት ከመንፈቅ ትብለጠዉ እንጂ ገና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች ዉብ የአኝዋክ ኮረዳ ናት። ማጂን አጎጠጎጤ ጡቶቿና ፈገግ ባለች ቁጥር ምሽቱን ወደ ንጋት የመለወጥ ችሎታ ያላቸዉ ነጫጭ ጥርሶቿ በአጭር ሊቀጫት ታጥቆ የመጣን የአግአዚ አዉሬ ቀርቶ መሽቶበት እቤታቸዉ ያደረ ቤተዘመድንም ያባብላሉ። ማጂን መልኳ ብቻ ሳይሆን በትምህርቷም የላቀ ዉጤት የምታመጣ ጎበዝ ተማሪ ናት። ታናሽ ወንድሟ አማኑኤል ደግሞ ትምህርት ለሱ ብቻ እሱም ለትምህርት የተፈጠረ የሚመስል ጓደኞቹ "ቀለሙ" ብለዉ የሚጠሩት እጅግ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነዉ። በከፊል እርሻና በከብት ርቢ የሚተዳደሩት ወላጆቻቸዉ አቶ አጋላ አሞትና እናታቸዉ ወይዘሮ አቻላ የትምህርትን እሴት ጠልቀዉ የተረዱ ሰዎች ስለሆኑ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ የተረፋቸዉን ጥሪት እንዳለ የሚያፈስሱት በሁለቱ ልጆቻቸዉ ትምህርት ላይ ነዉ። አማኑኤልና ማጂን ተወልደዉ ያደጉባት ፖቻላ እነዚህን ወንድምና እህት የምታዉቃቸዉ በትምህርት ጉብዝናቸዉ፤ በታዛዥነታቸዉና በቤ/ክርስቲያን አገልግሎታቸዉ ነዉ። በእርግጥም አማኑኤልና ማጂን የፖቻላ ቤተል ወንጌላዊት ቤ/ክርስቲያን ወጣት መዘምራን ናቸዉ።

ግን አማኑኤልና ማጅን ወጣትነታቸዉ፤ ጉብዝናቸዉ፤ ዝማሬያቸዉ፤ የወደፊት ተስፋነታቸዉና ሁሉም ነገራቸዉ እንዳለ በነበር ቀርቷል። እነዚህን ድፍን ፖቻላና አካባቢዉ ዬት ይደርሳሉ ብሎ በተስፋ ይጠብቃቸዉ የነበረ ወንድምና እህት ዛሬ ማንም የሚያስታዉሳቸዉ ሰዉ የለም። ወላጆቻቸዉም በነበር ቀርተዋልና አማኑኤልንና ማጂን አባትና እናታቸዉም አያስተዉሷቸዉም። የአኝዋክ ህዘብ በባህሉ ልጆቹን አይረሳም፤ በአኝዋክ ባህል ደግሞ ልጅ የሚባለዉ መንደርተኛዉ ሁሉ ነዉ። ሆኖም የወያኔ ዘረኞች አኝዋክን የቀሙት መሬቱን ብቻ ሳይሆን ባህሉን፤ ወጉንና የንግግር መብቱን ጭምር ስለሆነ አኝዋክ ወያኔ የጨፈጨፋቸዉን ልጆቹን ባሰበና በዘከረ ቁጥር የእሱም ዕጣ ፋንታ መጨፍጨፍ ስለሆነ ለግዜዉም ቢሆን ሙታን ልጆቹን መዘከር አቁሟል።

ታህሳስ አራት 1996 ዓም ዕለቱ ቅዳሜ ነበር። ቅዳሜ ቅዳሜ አማኑኤል፤ እህቱ፤ አባቱና እናቱ ቤታቸዉ ዉስጥ የሚሰራ ካለ የየድራሻቸዉን እየሰሩ፤ እያወጉ፤ እየበሉና እየጠጡ አንድ ላይ የሚሆኑበት ግዜ ነዉ። የነአማኑኤል ቤተሰብ ዕለተ ቅዳሜ ታህሳስ አራትን ያሳለፈዉ ይህንኑ የተለመደዉን የቤተሰቡን ልማድ ተከትሎ ነበር። የምሳ ሰአት ሲደርስ ቤተሰቡ ምሳ አንድ ላይ በላና አማኑኤልና ማጂን የመዝሙር ልምምድ ስላለባቸዉ ወደ ቤ/ክርሲቲያን ሄዱ። ወላጆቻቸዉ ደግሞ አንዱ ቤት ሲያጸዳ ሌላዉ የተሰበረ እየጠገነ ሁለቱም በየግል ስራቸዉ ላይ አተኮሩ። ቀኑ እያጠረና እየመሸ በሄደ ቁጥር . . . . ዛሬ ልጆቹ ምን ነካቸዉ እያሉ ከመስጋርት በቀር የአማኑኤልና የማጂን ወላጆች ልጆቻችንን እንደገና አናይም የሚል ጥርጣሬ አጠገባቸዉም አልነበርም። ሁለቱ ልጆቻቸዉም ቢሆኑ የመዝሙር ልምምዳችንን ጨርሰን መቼ አባዬና እማዬጋ እንሄዳለን የሚል ጉጉት እንጂ ወላጆቻቸዉንና ያቺን ያደጉባትን ጎጆ እንደገና አናይም ብለዉ አስበዉም አያዉቁም ። አማኑኤልና ማጂንም ሆኑ ወደዚህ አለም ያመጧቸዉ ወላጆቻቸዉ የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት አረጋገጥኩ ብሎ የማለላቸዉ የወያኔ አገዛዝ አኝዋክ ስለሆኑ ብቻ ተወልደዉ እንዳደጉበት እንደ ጋምቤላ ጫካ ጨፍጭፎ ያጠፉናል ብለዉ በፍጹም አልጠረጠሩም።

የፖቻላ ቤቴል አማኑኤል ቤ/ክርስቲያን ፓስተር ሁሌም እንደሚያደርጉት ቅዳሜ ታህሳስ አራት 1996 ዓም ቢሯቸዉ ገብተዉ ስራቸዉን እየሰሩ ነዉ። ትኩረታቸዉ በነገታዉ እሁድ ስለሚያሰተምሩት ሰንበት ትምህርት ቢሆንም ከተዘጋዉ በር ጀርባ የሚመጣዉ የመዝሙር ቃና ቀልባቸዉን የሳበዉ ይመስላል። ፓስተር ኡጁሉ የተቀመጡበት ወንበር ላይ አንደገና ተደላድለዉ ተቀመጡና . . . . . መዝሙሩን ነገ መስማቴ አይቀርም ምነዉ ስራዬን ብጨርስ ብለዉ አይናቸዉንም ሃሳባቸዉንም መ/ቅዱሳቸዉ ላይ አደረጉ። የቤ/ክርስቲያኑ አዳራሽ ዉስጥ አማኑኤል፤ ማጂና ጓደኞቻቸዉ የመዝሙር ልምምዳቸዉን እንደቀጠሉ ነዉ። ፓስተር ኡጁሉም መዝሙሩን ነገ እሰማለሁ ባሉት ዉሳኔያቸዉ ፀንተዉ የሰንበት ትምህርት ዝግጅታቸዉን ተያይዘዉታል። "ሁሉን ነገር በተስፋ ጠብቁ" የሚለዉን የፈጣሪ ቃል አምነዉ ነገን በተስፋ የሚጠባበቁት ፓስተር ኡጁሉ የእሳቸዉ ነገ ከዛሬ እንደማያልፍ የሚያመልኩት ፈጣሪ አልነገራቸዉም እሳቸዉም ያወቁ አይመስልም።

ፓስተር ኡጁሉ የሰንበት ትምህርት ዝግጅታቸዉን እንደጨረሱ ወደ በቤታቸዉ ከመሄዳቸዉ በፊት ሁሌ እንደሚያደርጉት መንገዳቸዉን ለእግዚአብሔር አምላካቸዉ አደራ ለመስጠት ተንበረከኩ። ከፓስተር ኡጁሉ አፍ የመጀመሪያዉ የፀሎት ቃል ሲወጣና የቤ/ክርስቲያኑ የፊት ለፊት በር ተበርግዶ የወያኔ ታጣቂዎች እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታ ላይ መሳሪያቸዉን ሲያቀባብሉ የወጣዉ ድምጽ አንድ ላይ ተሰማ። ክላሺንኮቭ ጠመንጃቸዉን የደገኑ አራት ወታደሮች እጃቸዉ ላይ መ/ቅዱስ ብቻ የያዙትን ፓስተር ለፀሎት ከተንበረከኩበት አስነስተዉ ማዋከብ ጀመሩ . . . . . እኔኮ የእግዚአብሄር አገልጋይ ፓስተር ነኝ . . . . አሉ ወያኔ የሚፈልጋቸዉ ፓስተር በመሆናቸዉ ሳይሆን አኝዋክ በመሆናቸዉ መሆኑን ያልጠረጠሩት ፓስተር ኡጁሉ። ክላሺንኮቭ በታቀፉ የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች የተከበቡት የፓስተር ኡጁሉ ፊት አሁንም ፈገግታ አልተለየዉም፤ ከፊታቸዉ የሚነበበዉ ትህትናና እግዚአብሄር ያስተማራቸዉ ፍቅር እንጂ ጥላቻና ፍርሃት እንዳልሆነ በግልጽ ይታያል። . . . . . . ቅደም አንተን ነዉ የምንፈልገዉ አለ . . . . የአማርኛ ቃላት አደራደሩ የትግራይ ተወላጅ መሆኑን የሚያሳብቅበት የነፍሰ ገዳይ ቡድኑ መሪ። ፓስተር ኡጁሉ ከተንበረከኩበት ሳይነሱ . . . እሺ ምንም ችግር የለም ሂድ ወዳላቸሁኝ ቦታ ሁሉ እሄዳለሁ ግን እባካችሁ ፀሎቴን ልጨርስ ግዜ ስጡኝ ብለዉ የቡድኑን መሪ ለመኑት። የሚሰማህ ካለ ጸልይ አላቸዉና ጓኞቹን ይዞ ወደ ዉጭ ወጣ።

ፓስተር ኡጁሉ ቀና ብለዉ ሲመለከቱ የቤ/ክርስቲያኑ ግማሽ ተቃጥሎ እሳቱ እሳቸዉ ወዳሉበት እየመጣ ነዉ። ክፋትና ጭካኔ መታወቂያ ካርዳቸዉ የሆነዉ የአግአዚ ነፍሰገዳዮች ቤ/ክርስቲያኑ ላይ ቦምብ ከወረወሩ በኋላ የፓስተሩን መጨረሻ ለማየት በርቀት ተደርድረዉ ቆመዋል። የእሳቸዉ ህይወት ሳይሆን የወጣት መዘምራኑ ህይወት ያሳሰባቸዉ ፓስተር በእሳቱ መሀል ሮጠዉ መዘምራኑ የነበሩበት ክፍል ሲደርሱ የክፍሉን ዉስጥና ዉጭ መለየት አቃታቸዉ። ያ ለአመታት የእግዚአብሄርን ቃል ያስተማሩበት ቤ/ክርስቲያን ተቃጥሎ የቀረዉ ነገር ቢኖር እሳቱ ለብልቦ ያለፈዉ አልፎ አልፎ የቆመዉ ማገር ብቻ ነበር። ከሚቃጠለዉ እሳት ዉስጥ እንደሚመዘዝ ሀረግ እየተንቦገቦገ የሚወጣዉ ወላፋን ለብልቦ የፈጃቸዉ ፓስተር ኡጁሉ እራሳቸዉን ለማዳን እየሮጡ የቤታቸዉን አቅጣጫ መፈለግ ጀመሩ። ሆኖም ብዙም ሳይጓዙ አድፍጦ ይጠባበቃቸዉ የነበረዉ የወያኔ ገዳይ ቡድን የ41 አመቱን ፓስተር በሳንጃ ከታተፏቸዉ። ከአንድ ሳምንት በኋላ የሚቾች አስክሬን ከየቦታዉ ሲሰበሰብ የፓስተር ኡጁሉ አስከሬን የተለየዉ አጠገባቸዉ በነበረዉ ወርቃማ መስቀልና በጋብቻ ቀለበታቸዉ ነዉ እንጂ ወያኔማ እንኳን በአይን በዘመናዊ መሳሪያም ማንነታቸዉ እንዳይተወቅ እንደ ክትፎ ነበር የከተፋቸዉ።

ከወያኔ አልሞ ተኳሾች ጠመንጃ አፈሙዝ የሚወጠዉ ባሩድና ጭስ ከተፈጥሮ መዐዛ ዉጭ ሌላ ምንም ሽታ የማያዉቀዉን የፖቻላን አየር በክሎት አፉንጫ ማሽተት አይን ማየት ተስኖታል። አማኑኤልና መዘምራን ጓደኞቹ ሽሽት ከያዙ ግማሽ ሰዐት ያለፈ ሲሆን የአማኑኤል እህት ማጂና ሌሎቹ መዘምራን አንድ ላይ ሲሆኑ አማኑኤል ግን ከእነሱ ጋር አልነበረም። ከምሽቱ አስራሁለት ሰዐት ተኩል ሲሆን አካባቢዉን ሲያስስ የነበረዉ የወያኔ ገዳይ ቡድን መዘምራኑ የተሸሸጉበትን ቦታ ከበበ። ወዲያዉ ከመዝሙር ዉጭ መፈክር እንኳን ከአንደበታቸዉ ወጥቶ የማያዉቀዉን ወጣቶች ጨካኞቹ የወያኔ ወታደሮች በሰደፍና በቆመጥ መደብደብ ጀመሩ። የአማኑኤል እህት ማጂን ዱላ ሰዉነቷ ላይ አላረፈም፤ ሆኖም ማጂን የወያኔን ባለጌ ወታደሮች ፀባይ ሰምታለችና ሴት እሷ ብቻ በመሆኗ ሰዉነቷ በፍርሀት መንቀጥቀጥ ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ ማጂን የፈራችዉ ደረሰ። አንድ የወያኔ ወታደር እጇን ይዞ እየጎተተ ወደ ሰዋራ ቦታ ይዟት ሄደ። ወንድ የማታዉቀዉ ማጂን አንድ፤ ሀለትና ሦስት እያለ ተራ በተራ የሚመጠዉን የወያኔ አዉሬ ማስተናገዱ ታያትና እግሯም ልቧም አንድ ላይ ከዷት። መራመድም መተንፈስም አቃታት። እንደእናቷ ተድራ ወግ ማዕረጓን ለማየት ትጓጓ የነበረችዉ የማጂን የሴትነት ክብርና ንጽህና ህግና ስርዐት በማያዉቁ ህግ አስከባሪዎች ረከሰ። መዝሙር ልምምድ ብላ ከቤቷ የወጣቸዉ የአስራ አምስት አመቷ ማጂን እራሷን ስታ እራቁቷን መሬት ላይ ተጋድማለች። የወያኔ ወንጀለኞች አንዱ ሱሪዉን እየታጠቀ ሲመለስ ሌላዉ ሱሪዉን እየፈታ ይመጣል፤ ያልጠገበዉ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ይመላለሳል። ገና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰችዉ የ15 አመቷ ኮረዳ ማጂን እንደ ዘጠና አመት አሮጊት ሰዉነቷ እራሱን መሸከም አቅቶት ተልፈሰፈሰች፤ አነባች፤ አማጠች። መታጠቢያ ቤት ዉስጥ የቆመ ሰዉ እስከትመስል ድረስ ሰዉነቷ ላብ በላብ ሆነ። ግማሽ ሰዉነቷ በላብ ግማሹ በደም የተለወሰዉ ማጂን እራሷን ስታ በድን መሰለች።

ከአንድ ሰአት በላይ ሾክ ባለ ቁጥር ጉድባ ለጉድባ እየተደበቀ ሲሸሽ የቆየዉ አማኑኤል በድንገት ሳያዉቀዉ ከቀኑ 11 ሰአት ጀምሮ ሲሸሽና ሲደበቅ ከነበረዉ የወያኔ ነፍሰ ገዳይ ቡድን ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠ። አማኑኤል በጠመንጃዉ ጋጋታና የገዳይ ቡድኑ አባላት በሬድዮ በሚያደርጉት ንግግር ቢደናግጥም እራሱን እንደገዛ የአግአዚ መንጋ ጦር መሀል ጻጥ ብሎ ቆመ። ያ ፓስተር ኡጁሉን "የሚሰማህ ካለ ጸልይ" ብሎ ያማተበዉ የገዳዮቹ ቡድን መሪ . . . . . . ሂድና ከጓደኞችህ ጋር ተቀላቀል ብሎ እንደመብረቅ ጮኸበት። አማኑኤል ወደ ኋላዉ ዞሮ ሲመለከት መዘምራን ጓደኞቹ መሬት ላይ አንገታቸዉን ደፍተዉ ተኮልኩለዋል፤ እህቱ ማጂን ግን ከእነሱ ጋር አልነበረችም። አማኑኤል ሁለት እጆቹን እራሱ ላይ አድርጎ ......ማጂንስ? ብሎ ሲጮህና የመጨረሻዉን የወያኔ ባለጌ ማስተናገድ የተሳናት እህቱ ማጂን ጣረሞቷን ስትጮህ ድምጹና ድምጿ ገጠመ። . . . . ቁጭ በል አንተ ከልቢ........ ብሎ የአግአዚዉ አለቃ ክላሺንኮቩን አቀባበለ። አማኑኤል ግን የእህቱን የማጂንን የጣረሞት ድምጽ እንጂ የአግአዚን ትዕዛዝ ከቁብም አልቆጠረዉምና እየሮጠ የታላቅ እህቱን ድምጽ ወደሰማበት አቅጣጫ ሄደ። ማጂን በባለጌ ጓደኞቹ ስትደፈር እንደ ኢቲቪ ድራማ ቁጭ ብሎ ሲመለከት የነበረዉ የአግአዚ ወታደር ከተቀመጠበት ተነሳና አማኑኤል ላይ የጥይት እሩምታ አዘነበበት። ታላቅ እህቱን አድናለሁ ብሎ ሩጫ የጀመረዉ አማኑኤል እህቱ እግር ስር የመጨረሻዉን አየር ተነፈሰ። በጅግንነት የተጀመረዉ የወጣት አማኑኤል አጭር ታሪክ በጀግንነት ተደመደመ፤ . . . . . . ንታ ጓል ወዲእያ . . . . . ብሎ የገዳይ ቡድኑ መሪ ንግግሩን ሳይጨርስ አማኑኤልን የገደለዉ ወታደር ክላሺንኮቩ ላይ የተሰካዉን ሳንጃ ነቅሎ የማጂንን ጭንቅላትና ሰዉነት ለያየዉ። ምነዉ በገደሉኝ ብላ ስትጮህ የነበረችዉ ማጂን የወንድሟ የአማኑኤል ነፍስ የሰማይን በር ሳያንኳኳ ልድረስበት ብላ ተከተለችዉ።በአንድ አመት ተኩል ተለያይተዉ ወደዚህ አለም የመጡት አማኑኤልና ማጂን በሁለት ደቂቃዎች ልዩነት እቺን አለም ለቅቀዉ ሄዱ። ፖቻላን ለቅቀዉ ወደሚቀጥለዉ መንደር ለመሄድ በዝግጅት ላይ የነበሩት የወያኔ ወታደሮች የጥይት ድምጽ በአካባቢዉ እንዲሰማ ስላልፈለጉ የተቀሩትን የመዘምራን ቡድን አባላት ተራ በተራ ለድግስ እንደሚታረድ በሬ በቢለዋ አረዷቸዉ። ለሁለት አመት የፖቻላ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ምስረታን አስመልክቶ ጥምረት የደስታ መግለጫ መልዕክት አስተላለፈ

ባለፉት አርባ አመታት በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ምስረታና የትግል ሂደት ዉስጥ ጉልህ ሚና የተጫወቱና ግንባሩን ለረጂም ግዜ የመሩ የኦሮሞ ተወለጆች ከዚህ ቀደም ያራምዱት የነበረዉን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄ በመቀየር አዲሲቱንና ለሁለም እኩል የሆነች ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚደረገዉን ትግል ለመምራት የወሰዱትን እርምጃ በማድነቅ ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህን ለእኩልነት በኢትዮጵያ ለኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላላፈ። ጥምረት ይህንን የደስታ መግለጫ መልዕክት ያስተላለፈዉ በላፈዉ ሳምንት ማብቂያ ላይ አዲስ የተፈጠረዉ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ የመጀመሪያዉን ህዝባዊ ስብሳበ ለማድግ በዝግጅት ላይ በነበረበት ግዜ ነዉ። ይህንን ላለፉት አርባ አመታት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድባብ በአንድነት ኃይሎችና በብሄር ብሄረሰብ ሀይሎች ለሁለት ከፍሎ በአገሪቱ የለዉጥ ሂደት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳደረገ የሚነገርለትን የፖለተካ መስመር ቀይረዉ አዲስ ጉዞ የጀመሩት ሃይሎች እንደዚህ አይነቱን ታሪካዊና ስር ነቀል እርመጃ መዉሰድ የቻሉት ያሳለፉትን የትግል ታሪክ፤ የአሁኑን የኢትዮያ ተጨባጭ ሁኔታና የወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን መምሰል አለባት በሚሉ ግዙፍ ጥያቄዎች ላይ ለረጂም ግዜ ተወያየተዉ የጋራ ግንዛቤ ላይ ከደረሱ በኋላ መሆኑን ከግንባሩ ቃል አቀባይ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

እንደ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ግምት ይህ የአቋም ለዉጥ በኦሮሞ ማህበረሰብና በተለያዩ የፖለቲካ ሀይሎች ተቀባይንትን ካገኘ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ለረጂም ግዜ ሆድና ጀርባ ሆኑዉ የቆዩትን ሁለት ግዙፍ ሀይሎች በማቀናጀት የኢትዮጵን የፖለተካ ችግር በፍጥነት ይፈታል ብለዉ የሚያምኑ ብዙዎች ናቸዉ። “እኛ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር መስራቾች ለሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ፍትህ፤ነጻነት፤ እኩልነትና የዲሞክራሲ መብት መከበር መታገልን መሰረታዊ አላማዉ ያደረገ አዲስ የኦሮሞ የፖለቲካ ንቅናቄ መመስረቱን በይፋ እናበስራለን” ብሎ ከአንድ ሳምንት በፊት እራሱን ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ ያደረገዉ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር በዚህ መግለጫዉ ላይ ለኦሮሞ ህዝብ፤ ለመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ለኢያንዳንዳቸዉ የሚመለከታችዩን መልዕክት አስተላልፏል። የኦሮሞን ህዝብ ሚና በተመለከተ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ኢትዮጵያን ዲሞክራሲየዊ አገር በማድረጉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብሏል። ከዚህ በተጨማሪ ኦሮሞን ጨምሮ በሌሎች የአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ላይ የሚደርሰዉ ሰቆቃ፤ ጭቆና፤አድልዎ፤ እንግልት፤ ዉርደትና ብዝበዛ ከምን ግዜዉም በላይ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ይገኛል ካለ በኋላ ለሁሉም የአገሪቱ ህዝቦች ነጻነት እኩልነትና ዲሞክራሲ መብት መከበር መታገል የሚያስችለንን አዲስ የፖለቲአ ንቅናቄ የመሰረትነዉም በእንደዚህ አይነቱ የፖለቲካ ንቅናቄ ስር ተደራጅተን ብንታገል ለሁሉም የሚበጅ ዉጤት ለማስመዝገብ አርግጠኛ በመሆን ነዉ ብሏል።

ጥምረት ለኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር የላከዉን የደስታ መግለጫ መልዕክትና የግንባሩን መመስረት ተከትሎ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ዉስጥ ሊኖር የሚችለዉን የሀይል አሰላለፍና አብሮ መስራት አስመልክቶ ያናገርናቸዉ የጥምረቱ የዉጭ ዘርፍ ሀላፊ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ እንደገለጡት የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር መመስረትና በተለይም ይህ ግንባርና የዛሬ ሁለት አመት በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራዉ ኦነግ ያደረጉት ስር ነቀል ለዉጥ በተለያዩ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ለግማሽ ምዕተ አመት የዘለቀዉን ያለመተማመንና የፍርሀት ማነቆ በመስበር ሕዝባዊ ትግሉን ወደፊት ያራምደዋል ብላዋል። በተለይም ኢትዮጵያ ዉስጥ በተባበረ ህዝባዊ አመጽ የወያኔነ ዘረኛ ስርአት ለመደምሰስ የሚደረገዉ ትግል እስከዛሬ ድረስ አጥቶት የነበረዉን አጋር ስለሚያገኝ ይህ የተወሰደዉ የአቋም ለዉጥ ጥቅሙና ፋይዳዉ በስፋቱም በጥልቀቱም እጅግ በጣም ትልቅ ነዉ ብለዋል። አቶ ኤፍሬም ንግግራቸዉን በመቀጠል ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አንዱን ገንጣይ ሌላዉን አፍራሽኛ የዱሮ ስልጣን ናፋቂ እያለ ካሁን በኋላ ህዝብን ማታለልና መከፋፈል አይችልም ብለዋል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአማራ ተወላጆችን ማፈናቀሉን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሰፈሩበት ቦታ እስካሁን አልታወቀም። የተወሰኑ ተፈናቃዮች በከተሞች በልመና ላይ መሰመራታቸውን ለማወቅ ቢቻልም፣ ቁጥራቸው ከ20 ሺ የማያንሱ ተፈናቃዮች የሰፈሩበትም ቦታም ይሁን የደህንነታቸው ሁኔታ አልታወቀም።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቤንሻንጉል ጉሙዝ የተፈጸመው ኢሰብአዊ ድርጊት ከአገር ውስጥ አልፎ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ተቃውሞዎችን እያዘጋጁ ነው። በጀርመን አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ፣ ለአንድ ወር የሚቆይ የፊርማ ማሰባሰብ ስራ እየሰሩ ሲሆን፣ ተመሳሳይ ፊርማ የማሰባሰብ ስራም በኢንተርኔት እየተደረገ ነው።። እንዲሁም በስዊድን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የመንግስትን ፖሊሲ በመቃወም በስቶክሆልንም ከአራት ቀናት በሁዋላ ሚያዚያ 4 ወይም ኤፕሪል 12 የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚያደርጉ አስተባባሪዎቹ መግለጻቸው ታውቋል።

## በደል እንዴት ይረሳል!!

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቤተል ቤ/ክርሲቲያንን በመዝሙር ያገለገሉት ወጣቶች አንዱ የሌላዉን ስቃይ እየተመከተ አንድ በአንድ የወያኔ ሳንጃ እራት ሆኑ።

የሁለት ልጆቻቸዉ አለወትሮዉ መዘግየት ያሳሰባቸዉ የአማኑኤልና የማጂን ወላጆች አቶ አጋላና አና ወይዘሮ አቻላ ጎጂቸዉ ዉስጥ ቁጭ እንዳሉ አንዱ ሌላዉን በዝምታ ይመለከታል። አይኖቻቸዉ በተቁለጨለጩ ቁጥር አፋቸዉ ትንፍሽ ባይልም አይናቸዉ ግን አንዱ ሌላዉን . . . . .. እንዴ ሂድና ልጆቹን ፈልግ እንጂ የሚል ይመስላል። በቤተሰብ ፍቅር የሞቀችዉ የነአማኑኤል ጎጆ በድንገት በተፈጠረዉ ፍርሀትና ጥርጣሬ ቀዘቀዘች። አማኑኤልና ማጂን የሄዱት ለመዝሙር ልምምድ ወደ ቤ/ክርስቲያን ስለሆነና ደግሞም ሁለቱን ጨዋ ልጆቻቸዉን የመንደሩ ሰዉ ሁሉ እንደራሱ ልጅ ስለሚሳሳላቸዉ ወላጆቻቸዉ ለግዜዉ ቢሰጉም ዬት ገቡ ብለዉ ነዉ እንጂ ፖቻላን በመሰለ ሰዉም ከብቱም የመሸበት በሚያድርበት ሠላማዊ መንደር ዉስጥ አማኑኤልንና ማጂንን የሚጎዳ ፍጡር ይኖራል ብለዉ በፍጹም አልጠረጠሩም፤ . . . . . . ግን . . . . ምሽቱ ወደ ሌሊት በተለወጠ ቁጥር ስጋታቸዉና ጥርጣሬያቸዉ እየጨመረ መጣ፤ ደግሞም ወላጅ ናቸዉና የሁለቱም ልብና አይን ልጆቻቸዉን ለማየት ተርገበገበ። ሲከፋቸዉ እምባቸዉ የሚቀድመዉ ሆደ ቡቡዉ አቶ አጋላ ባለቤታቸዉን ላለማስደንገጥ ለሰአታት አምቀዉ የያዙት እምባ ከቁጥጥራቸዉ ዉጭ ሆነና ፊታቸዉን ሸፈነዉ። ወ/ሮ አቻላ ከተቀመጡበት ተነስተዉ ባለቤታቸዉን ለማጽናናት ሲሞክሩ አቶ አጋላ ቀድመዉ ተነሱና . . . . . አንቺ ቁጭ በይ እኔ ይዣቸዉ እመጣለሁ ብለዉ ከሰአታት በፊት ወደ ሰማይ ቤት ሩጫ የጀመሩትን ልጆቻቸዉን ፍለጋ በሩን ከፍተዉ ወጡ -

…. እንዴ! አንቺማ እቤት ቁጭ በይ እንጂ ……ከመሸ ቤት ባዶ አይተዉምኮ አሉ የአማኑኤል አባት ባለቤታቸዉ ቤቱን ዘግተዉ ሲከተሏቸዉ አይተዉ - ተወኝ እባክህ ለምን ቤት ሁኚ ትለኛለህ? . . . . አብረን እንዳመጣናቸዉ አብረን እንፈልጋቸዋለን … ቤቱኮ ቆየ ባዶ ከሆነ ብለዉ ባለቤታቸዉን ተከትለዉ ወጡ።

የሁለት ልጆቻቸዉ አለወትሮዉ መዘግየት ያሳሰባቸዉ የአማኑኤልና የማጂን ወላጆች አቶ አጋላና አና ወይዘሮ አቻላ ጎጂቸዉ ዉስጥ ቁጭ እንዳሉ አንዱ ሌላዉን በዝምታ ይመለከታል። አይኖቻቸዉ በተቁለጨለጩ ቁጥር አፋቸዉ ትንፍሽ ባይልም አይናቸዉ ግን አንዱ ሌላዉን . . . . .. እንዴ ሂድና ልጆቹን ፈልግ እንጂ የሚል ይመስላል። በቤተሰብ ፍቅር የሞቀችዉ የነአማኑኤል ጎጆ በድንገት በተፈጠረዉ ፍርሀትና ጥርጣሬ ቀዘቀዘች። አማኑኤልና ማጂን የሄዱት ለመዝሙር ልምምድ ወደ ቤ/ክርስቲያን ስለሆነና ደግሞም ሁለቱን ጨዋ ልጆቻቸዉን የመንደሩ ሰዉ ሁሉ እንደራሱ ልጅ ስለሚሳሳላቸዉ ወላጆቻቸዉ ለግዜዉ ቢሰጉም ዬት ገቡ ብለዉ ነዉ እንጂ ፖቻላን በመሰለ ሰዉም ከብቱም የመሸበት በሚያድርበት ሠላማዊ መንደር ዉስጥ አማኑኤልንና ማጂንን የሚጎዳ ፍጡር ይኖራል ብለዉ በፍጹም አልጠረጠሩም፤ . . . . . . ግን . . . . ምሽቱ ወደ ሌሊት በተለወጠ ቁጥር ስጋታቸዉና ጥርጣሬያቸዉ እየጨመረ መጣ፤ ደግሞም ወላጅ ናቸዉና የሁለቱም ልብና አይን ልጆቻቸዉን ለማየት ተርገበገበ። ሲከፋቸዉ እምባቸዉ የሚቀድመዉ ሆደ ቡቡዉ አቶ አጋላ ባለቤታቸዉን ላለማስደንገጥ ለሰአታት አምቀዉ የያዙት እምባ ከቁጥጥራቸዉ ዉጭ ሆነና ፊታቸዉን ሸፈነዉ። ወ/ሮ አቻላ ከተቀመጡበት ተነስተዉ ባለቤታቸዉን ለማጽናናት ሲሞክሩ አቶ አጋላ ቀድመዉ ተነሱና . . . . . አንቺ ቁጭ በይ እኔ ይዣቸዉ እመጣለሁ ብለዉ ከሰአታት በፊት ወደ ሰማይ ቤት ሩጫ የጀመሩትን ልጆቻቸዉን ፍለጋ በሩን ከፍተዉ ወጡ -

…. እንዴ! አንቺማ እቤት ቁጭ በይ እንጂ ……ከመሸ ቤት ባዶ አይተዉምኮ አሉ የአማኑኤል አባት ባለቤታቸዉ ቤቱን ዘግተዉ ሲከተሏቸዉ አይተዉ - ተወኝ እባክህ ለምን ቤት ሁኚ ትለኛለህ? . . . . አብረን እንዳመጣናቸዉ አብረን እንፈልጋቸዋለን … ቤቱኮ ቆየ ባዶ ከሆነ ብለዉ ባለቤታቸዉን ተከትለዉ ወጡ።

( ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

ውድ አንባቢዎቻችን
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org